የሰ/መ/ቁ 69821

ታህሳስ 17 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሤ

**አመልካች፡-** አቶ ጥላሁን ጎበዜ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** 1. አቶ መከተ ኃይሉ - ቀረቡ

2. አቶ አወቀ ሙጨ - በሌሉበት

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የገጠር የእርሻ መሬት ይዞታ ክርክር ሲሆን የተጀመረው በአማራ ብሔ/ክልላዊ መንግሥት በፎገራ ወረዳ ፍ/ቤት የአሁን አመልካች ባቀረበው ክስ የተጀመረ ነው፡፡ ቀርቦ የነበረውም ክስ ተከሣሾች በ1989 ዓ.ም በተደረገው የመሬት ሽግሽግ የተመራሁትን ስለያዙብኝ እንዲለቁልኝ በማለት አዋሣኙን በመጥቀስ እንዲወሰንለት ጠይቋል፡፡ ተከሣሾች በቀረበው ክስ ላይ መልስ እንዲሠጡበት ታዘው በሰጡት መልስ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው መሬት ከ1989 ዓ.ም. በፊትም የራሳቸው የነበረ ስለመሆኑ፣ በ1989 ዓ.ም. የመሬት ሽግሽግ ሲደረግ ለተከሣሾች የተቆጠረ ስለመሆኑ፣ በ1997 ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ የይዞታ ማረጋገጫ ተሰጥቷቸው የሚጠቀሙበት የራሳቸው ይዞታ በመሆኑ የቀረበው ክስ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የክልሉ የወረዳ ፍ/ቤት ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ ተከሣሾች በዚህ አከራካሪ በሆነው የእርሻ መሬት ላይ የይዞታ ማረጋገጫ ስለተሰጣቸው ያለአግባብ የተሰጠ የይዞታ መረጋገጫ ከሆነ ይዞታውን ለሰጠው አካል ከማቅረብ ውጭ በቀረበው ክስ መሬቱ የከሣሽ ነው በማለት ማስለቀቅ አይቻልም በማለት በእንደዚህ ዓይነት መልኩ ክስ መቅረቡ ህጋዊ አይደለም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሠኘት ይግባኙን ለደቡብ ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍርድ ቤቱ ጉዳዩ ያስቀርባል በማለት የግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የበታች ፍ/ቤት ውሣኔን በመሻር ተከሣሾች ለክርክር ምክንያት የሆነውን የእርሻ መሬት ለከሣሽ (አመልካች) እንዲያስረክቡ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪዎች በበኩላቸው በዚህ የክልሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ጉዳዩ ያስቀርባል በማለት የግራ ቀኙን ክርክር በመስማት የከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመሻር የወረዳውን ፍ/ቤት ውሣኔ በማጽናት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ የክልሉ የሰበር ሰሚ ችሎትም የክልሉ የጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ በአብላጫ ድምጽ በማጽናት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አሁን የቀረበው ቅሬታ በዚሁ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ የግራ ቀኙን ክርክር በጽሑፍ ሰምተናል፡፡ 2ኛ ተጠሪ ባለመቅረቡ መልስ የመስጠት መብቱ ታልፎአል፡፡ ችሎቱም የተነሱትን ክርክሮች፣ ከተያዘው ጭብጥና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የበታች ፍርድ ቤቶች በቀረበው ክስ ላይ ውሣኔ የሰጡት ተገቢውን የማጣራት ሂደት በማድረግ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ጭብጥ ተይዞ የተያዘው ጉዳይ እልባት ማግኘት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በአማራ ብሔ/ክልላዊ መንግሥት የገጠር መሬት አዋጅ ቁ. 133/98 አንቀጽ 24(4) እና ይሄንን አዋጅ ለማስፈጸም በወጣው የደንብ ቁጥር 51/99 አንቀጽ 20(4) የይዞታ ማረጋገጫ የያዘ ሰው የመሬቱ ባለይዞታ እንደሆነ እንደሚገመት ይደነግጋል፡፡ ይሄ ማለት ግን በህጉ የተቀመጠው የባለይዞታነት ግምት ሊስተባበል የማይቻል በራሱ ብቻ አሳሪ ማስረጃ ስለመሆኑ የተመለከተ ነገር የለም፡፡

በአንድ የፍትሐብሔር ክርክር በህጉ በተለየ ሁኔታ የማስረጃ አቀራረብ ሥርዓቱ የተገደበ ካልሆነ በጽሑፍ፣ በምስክር፣ በህሊና ግምት፣ በተከራካሪዎች እምነት፣ ወይም በመሓላ ማስረጃ ማስረዳት እንደሚቻል በፍተሐብሔር ህግ ቁ. 2002፣ 1195፣1196 እና በተለያዩ ህጎች ውስጥ የማስረጃ አቀራረብ ሥርዓቶችን የሚደነግጉ ድንጋጌዎች አጠቃላይ ዓላማ፣ ይዘትና መንፈስ መረዳት ይቻላል፡፡ በዚሁ መሠረት አመልካች ተከሣሾች ይዞታዬን ይዘውብኛል እና እንዲለቁልኝ ይወሰንልኝ በማለት ክስ ያቀረበ ሲሆን ተጠሪዎችም የራሳቸውን መከራከሪያና በ1997 ዓ.ም የተሰጣቸውን የይዞታ ማረጋገጫ አቅርበዋል፡፡ ይሄ በሚሆንበት ጊዜ ጉዳዩን የተመለከተው ፍርድ ቤት ግራ ቀኙ ያላቸውን ማስረጃ በመስማት እና ከሌላ የመንግሥት አካላትም መቅረብ ያለበትን ማስረጃ በመቀበልና የቀረቡትን ማስረጃዎች በማመዛዘን ተገቢውን ውሣኔ መስጠት ሲገባው ተጠሪዎች የይዞታ ማረጋገጫ ያቀረቡ በመሆኑ የቀረበው ክስ ተቀባይነት የለውም በማለት ውሣኔ መስጠቱ አግባብነት የለውም፡፡ የይዞታ ማረጋገጫም ቢሆን እንደአንድ ማስረጃ ተቀባይነት ያለውና ሊመዘን የሚችል እንጂ ወሣኝ (conclusive evidence) ባለመሆኑ ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ በመቀበል እና ሌሎች አስፈላጊ ናቸው የሚላቸውን ማስረጃዎች በመቀበል ተገቢውን ውሣኔ መስጠት ሲገባ የይዞታ ማረጋገጫ ሊስተባበል እንደማይቻል ማስረጃ በመውሰድ እንደዚሁም መስተባበል ካለበት የይዞታ ማረጋገጫውን ለሰጠው አካል አቤቱታ በማቅረብ ብቻ እንደሆነና ፍርድ ቤቱ በግራቀኙ ማስረጃ ጉዳዩን ተመልክቶ የመወሰን ስልጣን እንደሌለው በመውሰድ የቀረበውን ክስ ህጋዊ አይደለም በማለት ውሣኔ መስጠቱ አግባብነት የለውም፡፡

በሌላ በኩል ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የደቡብ ጎንደር ከፍተኛ ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ ያስቀርባል አያስቀርብም በማለት ተገቢውን ትዕዛዝ ከመስጠቱ በፊት ለተጠሪዎች የተሰጠውን የይዞታ ማረጋገጫ የተሰጠበትን አግባብ የወረዳው የመሬት አስተዳደር አካል መግለጫ እንዲሰጥበት ማድረጉ ተጠሪዎች የክርክሩ አካል ባልተደረጉበት ጊዜ በመሆኑ አግባብነት ያለው የማስረጃ አሰባሰብ ስርአት ያልተከተለ በመሆኑ ተቀባይነት ያለው አይደለም ብለናል፡፡ ምክንያቱም ማጣራቱ ተገቢ መሆኑን ፍርድ ቤቱ ካመነበት ግራቀኙ የክርክሩ አካል በሆኑበትና የእኩልነት መርህን በጠበቀ መልኩ መከታተልና በቀረበው ማስረጃ ላይ አስተያዬት መስጠት በሚችሉበት ሁኔታ መደረግ ነበረበት፡፡

ባጠቃላይ የበታች ፍርድ ቤቶች ለክርክሩ ምክንያት የሆነው የእርሻ መሬት የማን ይዞታ ነው? የሚለውን ነጥብ በግራቀኙ ማስረጃ በማጣራት እንደዚሁም ከሌላ የመንግስት አካልም ተጨማሪ ማስረጃ መቀበል አስፈላጊ ከሆነም ይሄው ስርአት ተፈፅሞ የተያዘው ጉዳይ እልባት ማግኘት ሲገባው መሰረታዊ የማስረጃ አቀባበልና ምዘና ስርአት ባልተከተለ መልኩ የተሰጠው ውሣኔ አግባብነት የሌለውና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የአማራ ብሔ/ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ሰሚ ችሎት የመዝ.ቁ. 07860 ሚያዝያ 24 ቀን 2003ዓ.ም በዋለው ችሎት፣የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመዝ.ቁ.25228 በቀን 03-7-2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት፣ የደቡብ ጎንደር መስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝ.ቁ. 21099 በቀን 11-10-2003 ዓ.ም. በዋለው ችሎት እና የፎገራ ወረዳ ፍ/ቤት መዝ.ቁጥር ባልተጠቀሰ በቀን 15-4-2001 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጡት ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪዎች ለክርክሩ ምክንያት በሆነው የእርሻ መሬት ላይ የይዞታ ማረጋገጫ በመያዛቸው ብቻ ሊስተባበል አይችልም በማለት የቀረበውን ክስ ውድቅ ማድረጋቸው አግባብነት ያለው አካሄድ አይደለም ብለናል፡፡ በመሆኑም የፎገራ ወረዳ ፍ/ቤት ግራቀኙ አከራካሪ በሆነው የእርሻ መሬት ላይ ያላቸውን ማስረጃ መስማትና ሌሎች ተገቢ ናቸው የሚለውን ተጨማሪ ማስረጃዎች ከሚመለከተው የመንግስት አካል በማጣራት ተገቢውን ውሣኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 343/1/ መሰረት መልሰንለታል፡፡
3. በዚህ ችሎት በተደረገው ክርክር በግራቀኙ ለደረሰው ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሐ/አ